ቁጥር ፀፍAG-F-04-8/2/12
ቀን- 17/7/2012

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

**ለአቶ አርአያ ገ/እግዛብሄር**

**የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ**

**<u>አዲስ አበባ</u>**

ጉዳዩ ፡ <u>የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣</u>

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰው ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 4 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ 13 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች እና 20 ገፅ የሂሳብ ሪፖርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

**ሠይፉ ከበደ**
**የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት**

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ የፌዴራል

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኤጀንሲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል። ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል።

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኤጀንሲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች

__የተከፋይ ሂሳብ፣__

4. በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 61,591,701.79 በተከፋይ ተይዞ መገኘቱና፣ ተከፋይ ሂሳቦቹ በተከፋይ የተያዘበትን ቀንና ዓ.ም፣ የሚከፈልበትን ጊዜ እና የሚከፈለውን ባለመብት ድርጅት ወይም ግለሰብ የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ ባለመቅረቡ ሂሳቡ ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ እና ለማን እንደሚከፈል ለማረጋገጥ አልተቻለም።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም.የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክልያሳያሉ በማለት አስተያየት መስጠት አልተቻለም።

__ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣__

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

- በበጀት ዓመቱ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣ ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 456,295,419.44 ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱን፣

__ሌሎች ጉዳዮች፣__

- በኤጀንሲው የ2011 በጀት ዓመት ዓመታዊ የቋሚ ንብረት ቆጠራ ያልተደረገ እና ከንብረት ምዝገባ ጋር ያልታረቀ መሆኑን፣
- አግልግሎት የማይሰጡ ጎማዎች፣ ኮምፒዩተሮች፣ የተለያዩ ወንበሮች፣ አሮጌ ሽራዎች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ፕሪንተሮች፣ የእንጨት መደርደሪዎች፣ የፈተና ማረሚያ ማሽኖች እና Ups ከዕቃ ማስቀመጫ መጋዘን ውስጥ ተቀምጠው መገኘታቸው፣
- ኤጀንሲው በ2011 በጀት ዓመት በእቅድ መሰረት የ4ኛ ሩብ አመት ሪፖርት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ያልወጣ መሆኑን፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤ